መግለጥ እና ምሪት



ትምህርት 5 ለጥቅምት
21/ 2019

“ቶሎ ይሆን ዘንድ የሚገባውን ነገር ለባሪያዎቹ ያሳይ ዘንድ እግዚአብሔር ለኢየሱስ ክርስቶስ የሰጠው በእርሱም የተገለጠው ይህ ነው፥ ኢየሱስም በመልአኩ ልኮ ለባሪያው ለዮሐንስ አመለከተ፥ እርሱም ለእግዚአብሔር ቃልና ለኢየሱስ ክርስቶስ ምስክር ላየውም ሁሉ መሰከረ።” (ራዕይ 1:1-2)



ራዕይ ምዕራፍ 1:1-2 እግዚአብሔር በነቢዩ መልዕክቱን ሲገልጥ የምናይበት አንዱ ምሳሌ ነው:

እግዚአብሔር መልዕክቱን ለኢየሱስ ገለጠለት → ኢየሱስ መልዕክቱን ለመልዓኩ ገለጠለት → መልዓኩ መልዕክቱን ለነቢዩ ዮሐንስ ገለጠት → ዮሐንስ የተቀበለውን መልዕክት በጽሁፍ አስቀመጠው




እግዚአብሔር ግን ለነቢያቱ እራሱን የሚገልጥበት መንገድ ወይም መለኮታዊ መልዕክቱን በእነርሱ በኩል የሚያስተላልፈው በዚህ መንገድ ብቻ አይደለም። እግዚአብሔር ለነቢያቱ እራሱን የገለጠበትና ምሪትን የሰጠባቸውን ልዩ ልዩ መንገዶችን በዚህ ትምህርት እናጠናለን።



- መገለጥ እና ምሪት:
  - አጠቃላይ እና ልዩ መገለጥ
  - የምሪት ሂደት
- የትንቢታዊ መልዕክቶች አይነት:
  - የቃል መልዕክቶች
  - የጽሁፍ መልዕክቶች
  - ትዕይንቶች፣ ተምሳሌቶችና ምሳሌዎች



መገለጥ እና ምሪት



አጠቃላይ እና ልዩ መገለጥ

"ሰማያት የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ፥ የሰማይም ጠፈር የእጁን ሥራ ያወራል።"
(መዝሙር 19:1)


"እርሱም፦ ቃሌን ስሙ፤ በመካከላችሁ ነቢይ ቢኖር፥ እኔ እግዚአብሔር በራእይ እገለጥለታለሁ፥ ወይም በሕልም እናገረዋለሁ።"
(ዘኍልቅ 12:6)



የእግዚአብሔርን መኖር የሚክዱ ሰዎች "የማይታየው የእግዚአብሔር ባሕርይ፣ ይኸውም ዘላለማዊ ኀይሉና መለኮትነቱ" በፍጥረቱ ስለተገለጠ "ማመካኛ የላቸውም" ሲል ጳውሎስ ይናገራል (ሮሜ 1:20፣ መዝ 19:1)።

እግዚአብሔር በፍጥረቱ ውስጥ የመታደስን ኃይል ማስቀመጡ እንኳ የኃጥያትን መግባት አስቀድሞ በማየት መፍትሄ ማዘጋጀቱን ያሳየናል። አካላችን ሲቆስል ቁስሉን ለመሻርና ህዋሶቹን ለማደስ ህዋሶቻችን መንቀሳቀስ ይጀምራሉ። እነዚህ የህዋሳት ስርዓቶች ጉዳት ሳይደርስብን በፊት የተቀመጡ ናቸው!

ነገር ግን ከአዳምና ሔዋን ወድቀት በኋላ ተፈጥሮ በኃጥያት ውጤቶች ተጎሳቁሏል (መገዳደል፣ መሬት መንቀጥቀጥ ...)



እግዚአብሔር በዚህ ምክንያት እራሱን ለመግለጥ በይበልጥ ቀጥተኛ መንገዶችን መርጧል። ይህም መገለጥ ልዩ መገለጥ በመባል ሲታወቅ እግዚአብሔር በነቢያት በኩል በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ እንደ ተዘገበልን በቃሉ ተገልጦ እናገኘዋለን፤ በመጨረሻም በልጁ በኢየሱስ ሚስጥሩን ገልጦልናል (ዕብ 1:1-2)።



የምሪት ሂደት

"ቅዱሳት መጻሕፍት ሁሉ የእግዚአብሔር እስትንፋስ ያለባቸው ናቸው፤ ለማስተማር፣ ለመገሠጽ፣ ለማቅናት በጽድቅም መንገድ ለመምከር ይጠቅማሉ፤" (2 ጢሞቴዎስ 3:16)



እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለመጀመሪያ ጊዜ ሥራውንና ቃሉን እንዲመዘገብ እስካደረገበት ጊዜ ድረስ የእግዚአብሔር ሥራዎችና መልዕክቶች ለብዙ ምዕተ ዓመታት በቃል ከትውልድ ወደ ትውልድ ሲተላለፉ ቆይተው ነበር።



ከዚያን ጊዜ አንስቶ እግዚአብሔር ሊያሰፍራቸው የፈለጋቸውን መልዕክቶቹን በመንፈስ ቅዱስ "በተመሩ" ሰዎች እንዲፃፉ አድርጓል (2 ጴጥ 1:21)። መጽሐፍ ቅዱስ የመለኮታዊ መገለጥን በዚህ መልኩ በሙላት በመያዙ ልዩ ሥፍራ እንዲኖረው ሆኗል።

የምሪቱ ሂደት ምን ይመስል ነበር?



በራዕይ እና በህልም (ዘኁ 12:6)



በግል ልምምዶች (1 ዮሐ 1:3)



በታሪክ ጥናት (ሉቃ 1:3)



በመለኮታዊ ምሪት (2ጴጥ 1:21)








የትንቢታዊ መልዕክቶች አይነት

የቃል መልዕክቶች

"ይህንም ትእዛዝ እግዚአብሔር በነቢያቱ እጅ አዝዞአልና እንደ ዳዊትና እንደ ንጉሡ ባለ ራእይ እንደ ጋድ፥ እንደ ነቢዩም እንደ ናታን ትእዛዝ፥ ጸናጽልና በገና መሰንቆም አሰይዞ ሌዋውያንን በእግዚአብሔር ቤት አቆመ። ሌዋውያንም የዳዊትን የዜማ ዕቃ ይዘው፥ ካህናቱም መለከቱን ይዘው ቆመው ነበር።"(2 ዜና 29:25-26)

እግዚአብሔር በተለያዩ አራት ኢጋጣሚዎች ላይ ለሰዎች በቀጥታ ተናግሮ ያውቃል:



ለአዳም እና ለሔዋን (ዘፍ 2:16-17)



10ቱን ትዕዛዛት በሰጠ ጊዜ (ዘዳ. 4:12)




በኢየሱስ ጥምቀት ጊዜ (ማቴ 3:17)



በመገለጥ ተራራ ላይ (ማር 9:7)

ነቢያት ደግሞ እግዚአብሔር የሰጣቸውን መልዕክት "እግዚአብሔር እንዲህ ይላል" በማለት በቃላቸው ያስተላልፉ ነበር (መሳ 6:8)። ልክ እንደ ኖኅ መልዕክት በመጽሐፍ ተዘግበው ያሉ የነቢያት መልዕክቶች ቢኖሩም ያልተመዘገቡ መልዕክቶች ግን እንዳሉ ልንዘነጋ አይገባም።



የብዙ ነቢያትን ቃል ያወቅነው ሌሎች ሰዎች በጻፉላቸው ጽሁፍ ነው። ከእነዚህም መካከል ናታን፣ ኤልያስ፣ ኤልሳዕ እና መጥምቁ ዮሐንስ ይካተቱበታል። ነገር ግን የራሳቸውን መልዕክቶች በጽሁፍ ካሰፈሩት ነቢያት እኩል ሥልጣን አላቸው።





የጽሁፍ መልዕክቶች

"እግዚአብሔርም ሙሴን፦ ... ይህን ለመታሰቢያ በመጽሐፍ ጻፈው፥ ... አለው።" (ዘጸአት 17:14)

እግዚአብሔር መልዕክቱን በጽሁፍ ለማስፈር የወሰነባቸው አንዳንድ ምክንያቶች ምን ምን ናቸው?

- ክስተቶቹን ለማስታወስ (ዘጸ 17:14)
- እኛን ለማስተማር (መክ 12:10)
- እኛን ወደ ንስሃ ለመምራት (ኤር 36:2-3)
- መከተል ወይም መተው ያለብንን ምሳሌዎች እንድንመለከት (1 ዜና 10:11)
- የወደፊቱን እንድናውቅ (ራዕ 1:19)



በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ነቢያት የእራሳቸውንና የሌሎችን ሰዎች ምላሽ ገልጸው ነበር። ግጥሞችን፣ የታሪክ መዛግብትንና የተፃፉ ስብከቶችን አስፍረውልናል። አንዳንድ ጊዜ ከመጽሐፍ ቅዱስ ውጪ የሆኑ ጸሐፊያን ወይም የአሕዛብ ነገስታት አዋጅ ተጠቅሰው እናገኛለን።

ቢሆንም ግን በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ምሪት በደረጃ የተከፋፈለ አይደለም። የተመዘገቡት ስብከቶች፣ ክስተቶች ወይም ትንቢቶች ሁሉ በእግዚአብሔር ምሪት የተፃፉና በታሪክ ውስጥ በታማኝነት የተላለፉ የእግዚአብሔር መልዕክቶች ናቸው (2 ጢሞ 3:16-17)።

ትዕይንቶች፣ ተምሳሌቶችና ምሳሌዎች

"ለነቢያት ተናገርሁ፤ ራዕይንም አበዛሁላቸው፤ በእነርሱም በኩል በምሳሌ ተናገርሁ።" (ሆሴዕ 12:10)



ትዕይንት



መጽሐፍ ቅዱስ ከታሪክ መዛግብት፣ ከምሳሌያዊ አነጋገሮች፣ ግጥሞችና ንግግሮችም በተጨማሪ በትርዒቶች፣ በተምሳሌቶችና በምሳሌዎች ብዙ መልዕክቶችን ያስተላልፋል።

ሕዝ 4:1-8. እግዚአብሔር ሕዝቅኤልን የኢየሩሳሌም ከተማን ምሳሌ ሰርቶ መከበቧንና መፍረሷን እንዲያሳይ ጠይቆት ነበር።

ሆሴ 1:2-9. እግዚአብሔር ሆሴዕ አመንዝራ ሴትን እንዲያገባ አዝዞት የእስራኤልን ክህደት እንዲያሳይ አድርጎት ነበር።

1 ነገ 20:37-42. አንድ ነቢይ ሌላ ነቢይን እንዲመታው ጠይቆ በጦርነት የቆሰለ በማስመሰል የአካብን ኃጥያት ገስፆ ነበር።

ኤር 13:1-11. በእግዚአብሔር ትዕዛዝ ኤርምያስ መታጠቂያን ገዝቶ ከዚያም በጭቃ ውስጥ ሸሽጎት ነበር። ቀጥሎም እግዚአብሔር የኢየሩሳሌምን የሥነ ምግባር መዝቀጥ ለማሳየት መታጠቂያውን መልሶ እንዲያወጣው ነግሮት ነበር።









ትዕይንቶች፣ ተምሳሌቶችና ምሳሌዎች

ተምሳሌቶች







ዘጸ 25:8. ካህናቱ፣ ቤተመቅደሱና አገልግሎቶቹ የመዳንን ሥራ ዝርዝር የሚያስረዱ ተምሳሌቶች ናቸው።

ራዕይ 13:2. ዳንኤልና ራዕይ እንደ አውሬና ቀንዶች ያሉ ተምሳሌቶችን በመጠቀም የታሪክ እውነታዎችን በተምሳሌት ያቀርባሉ።

ዮሐ 15:1. ኢየሱስ ተልዕኮውን ለማስረዳት እንደ ብርሃን፣ የወይኑ ግንድና መልካሙ እረኛ የመሳሰሉትን ተምሳሌቶች ይጠቀም ነበር።





ምሳሌዎች

ኢሳ 5:1-7. ነቢያት ሕዝቡን የመንፈሳዊ ሁኔታቸው ላይ እንዲያሰላስሉ ምሳሌዎችን ይጠቀሙ ነበር።

ማቴ 13:5. ኢየሱስ መንፈሳዊ እውነቶችን ለማስተማር ምሳሌዎችን በብዛት ይጠቀም ነበር።

“መጽሐፍ ቅዱስ እውነትን ለተራቡ ልቦች በቀላሉና ፍጹም በሚገጥም መንገድ የሚገልጥ ሲሆን እጅግ የበለጸጉትን አእምሮዎች የሚያስደንቅና የሚማርክ ብቻ ሳይሆን ያነሱትንና ያልበለጸጉትን ደግሞ የመዳንን መንገድ እንዲለዩ የሚያስችል ነው። [...] ስለዚህም እግዚአብሔር ለመዳን በወሰነው መንገድ እያንዳንዱ ነፍስ የሚወስደውን እርምጃ እያስተዋለ ወደ እግዚአብሔር በንስሃ ወደ ጌታችን ኢየሱስ ደግሞ በእምነት እንዲያቀና መንገዱ ለሁሉም ተከፍቷል። [...] አንድ ሰው[ገጽ 108] መጽሐፍ ቅዱስን በይልጥ በመረመረ ቁጥር ሕያው የእግዚአብሔር ቃል መሆኑንና በመለኮታዊ መገለጥ ፊት የሰው አመክኖአዊነት ዝቅ ሊል እንደሚገባው እየተረዳ ይሄዳል።”

EGW (Steps to Christ, p. 107)

አባሪ: መገለጥ እና ምሪት በኤለን ኋይት



ኤለን ኋይት በመለኮታዊ ምሪት ያገለገለች ሰው ነች። ጽሁፎችዋ፣ ህይወቷ እና አገልግሎቷ እንደ እውነተኛ ነቢይ ነው። ከመጽሐፍ ቅዱስ ነቢያት እኩል ምሪት የነበራት ቢሆንም ጽሁፎችዋን ከመጽሐፍ ቅዱስ ጋር እኩል አድርጋ አስባቸው አታውቅም። መጽሐፍ ቅዱስን ሁልጊዜ ሥልጣን ያለውና የማይሳሳት የእግዚአብሔር መገለጥ አድርጋ ታቀርበዋለች።

የመለኮታዊ ምሪት ሂደት በመለኮትና በሰው መካከል ያለ ግንኙነትን እንደሚያካትት እውቅና ሰጥታ ነበር። እግዚአብሔር መልዕክቶቹን ለነቢይ ሲያስተላልፍ ነቢዩ ደግሞ የመለኮታዊ ምሪቱን በእራሱ ቃላት ተጠቅሞ ያስተላልፋል። መለኮታዊ ምሪት በሰው ሀሳብ ውስጥ ገብቶ ሲሰራ መለኮታዊ መገለጥና ሰብዓዊ ልምምድ እንደሚዋሃዱም ተረድታ ነበር።



ነገር ግን እርሷ ያስተላለፈቻቸው ልምምዶችና መረጃዎች ሙሉ በሙሉ በመለኮት የተመሩ እንዳልነበሩ ጠቁማ ነበር። ጽሁፎችዋንና ልምምዶችዋን ስንመለከት በተለይ ደግሞ ግለ ታሪኳንና ከሰዎች ጋር ያደረገቻቸውን ምልልሶች ስንመለከት ይህንን ከግምት ውስጥ ማስገባት ያስፈልገናል።



